የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No.6
ADDIS ABABA 3rd December, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፩/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ሦስት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ..........ገጽ ፮ሺ፮፻፷፯

CONTENTS

Proclamation No. 771/2012

International Development Association Financing Agreement for Promoting Basic Services Program-Phase III Project Ratification Proclamation ....... Page 6667

አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፩/፪ሺ፭

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ሦስት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፫፻፺፯ ሚሊዮን ፰፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ኦክቶበር ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፲፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No. 771/2012.

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 397,800,000 (Three Hundred Ninety Seven Million Eight Hundred Thousand Special Drawing Rights) for Promoting Basic Services Program Phase III Project was signed in Addis Ababa on the 8th day of October 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 22nd day of November 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

| ያንዱ ዋጋ Unit Price | 2.30 |
|---|---|

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ሦስት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፩/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ኦክቶበር ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ቁጥር 5162-ET ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫፻፺፯ ሚሊዮን ፰፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Promoting Basic Service Program – Phase III Project Ratification Proclamation No. 771/2012".

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit No. 5162-ET signed in Addis Ababa on the 18th day of October 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 397,800,000 SDR (Three Hundred Ninety Seven Million Eight Hundred Thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of December, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት